# ቅቤ አንጓቹ እሳቱ ከበደ!!

ሸለገ ራሱን፥ ለከርሱ ተገዛ
ሆድ አምላኩ እሳቱ ፤ እንዲህ እንደዋዛ::
እኛን በገደል ፤ ሕፃን ባስለቀሰ

ሕዝቡን በረሸነ፤ ደሙን ባፈሰሰ
አገር በቆረሰ ፤ ምድር በገመሰ
በዘር በከፈለ ፤ ወገን ባስጨረሰ
በንዲራ አዋርዶ፤ አገር ባሳነሰ
ሸማግሌ ሕፃኑን ፤ እምባ ባሳበሰ
በንዲህ ዓይነቱ ባንዳ ፤ በስሩ ትጠለል?

ዝግንን ስቅጥጥ አይልም ፤ እንደዚህ ስትቀል?
**ለእንዲህ ያለ መሰሪ**
**ለባንዳ ሊታዘን ፤ ለሸጠን ሊለቀስ**
**ባንዳ የባንዳ ልጅ፤ አይደለም ወይ መለስ!!**
**ሆዳም መለስ ሲሉ ፤አንተም መለስ ብትል**
**ለቡይ ጌታ አለው ፤ ለኃያልም ኃያል!!**

**በስሙ ልጠራ ፤ በግርማው ልጠለል**
**አፄ ሚኒሊክን ፤ እምዬን የሚያህል!!**
**እንዲያ እየተመመ ፤ ፈጥኖ የደረሰ**
**ፋሽስትን ደምስሶ ፤ ኢትዮጵያን ያደሰ::**
ዐባይ አላረገደ፤ ቁም ሲባል አልቆመ
ባንዳን አልታዘዝ ፤ ብሎ እየተመመ
ምድሩን እየገመሰ፤ እየደረመሰ
በፍጥነት ፈለሰ፤ እየተተኮሰ
መለስ አልል ብሎ፤ እየቀነጠረ
ቀነዝናዛው ዐባይ፤ እንዲያ እያመረረ

ውሎ አደሮ ወሰደው ፣ ካፈር ደባለቀው

ከከመረው ደለል፣ ክውስጡ ወሸቀው።

ያለ ዕረፍት ያለ እንቅልፍ ፣ ሰላም የነሳንን

ማነው አልሞተም እሚለን?

መለስ ደመኛችን ፣ እንደጠዋት ጤዛ ነው!!

**መለስ በገደለ ፣ መከራ ባሳየው**

**በርሃብ የተጎዳው ፣ አንጀቱ የታጠፈው**

**እሚጠጣ አጥቶ፣ ጎሮሮው የደረቀው**

**መቺ ሰትሮ ዐባይን ፣ጥሙን አስታገሰው**

**''እንደጠበል ጠድቅ ፣ ባርኮና ቀደሰው ''?**

**አንት ሸክሻካ ፣ አቀንቃኝ**

**ሸርካታ ስግብግብ ፣ ለሆዱ አላዛኝ**

እኔ ጀግና ልጥራ ፣ የሚጠለሉበት

አገሩን ያቆመ ፣ ለሕዝቡ የተሰዋለት

ካደባባይ ቆሞ መትረየስ ሳይፈራ፣እንቢ አገሬን ብሎ በሃይል እያቅራራ

ስጋሕን ለሚገል ጨርሶ እንዳትፈራ፣ ስጋሕንም ገሎ ንፍስሕን ለሚወስድ አምላክ ብቻ ፍራ

ብሎ ባንደበቱ እየተናገረ ፣አልረሸኑትም ወይ ኢትዮጵያን እያለ

ታሪኩ ሕያው ነው ፣ፍጻሜ የሌለው

ትውልድ ለትውልድ፣ የሚያስተላልፈው

**በስሙ ለጠራ ልምንሽነሽበት ፣ በመስቀሉ ጥላ ልጠለልበት**

**ጵጥሮስ አባታችን ፣ የምንኮራበት ።**

ዐባይ ሞገደኛ ፣ ዐባይ ማዕበል ነው

በዐባይ አይለመን ፣ ብር አይዛቅበት

ምንጣፍ አነጥፈው፣ ሳንቲም አይለቅሙበት

የድሃውን ደሞዝ ፣ እየጎመዱበት

ሕጻናት ተርበው፣መማር ተስኖአቸው

በዐባይ እየለመኑ ፣ከሲቃይ ከቶዋቸው

ስንቱን አስለቀሱ ፣ መክፈል አቅቶዋቸው::

እሳቱ ከበደ ሸክምህ የከበደ፣ሰብዓዊነት የሸጥክ

በዐመፃ የተወለድክ ፣ በትእቢት የተካንክ

በአውሬው ጥላ ስር ፣እራስክን የጠለልክ

አንት ሸክሻካ ፣ አቀንቃኝ

ሸርካታ ስግብግብ ፣ ለሆዱ አላዛኝ::

መይሳው ከምድረ ስዊድን 2012-09-22